## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15166 በህዳር 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37786 በህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ዳኝነት በጠየቁት መሠረት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር አመልካቾች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 29738

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአፓርትማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

ተጠሪ፡- ወ/ት ዘርአዳም አሰጋኸኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ ሥርዓት ህግን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች የሕብረት ቤት ስራ ማህበር ውስጥ በአባልነቴ ከተሰሩት ቤቶች መካከል ድርሻዬ የሆነውን ቤት የስራ አስፈጻሚ አባላት የሆኑት ግለሰቦች በወቅቱ ለእኔ ባለማስረከባቸው ምክንያት በቤቱ ላይ ለታየ ጉድለት ማሟያና ማሰሪያ ብር 80,000፣ /ሰማኒያ ሺህ ብር/ ቤቱን በወቅቱ ተረክቤ ቢሆን ኖሮ በማከራየት ላገኝ እችል የነበረውን ጥቅም ብር 24,000፣ /ሃያ አራት ሺህ ብር/ እንዲሁም ሌሎች ጉዳቶች በድምሩ 320,000/ሦስት መቶ ሃያ ሺህ ብር/ ሊከፍሉኝ የገባል በማለት በፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስ ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 የሚታገድ ከመሆኑም በላይ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? ጉዳዩ ከዚህ በፊት በውሳኔ ያለቀ ነው ወይ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ወገን ክሱን ማቅረብ ያለበት ጉዳቱ በደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን

እንዳለበት ስለሚደነግግና የአሁን ተጠሪ ደግሞ ክሱን ያቀረቡት ጉዳቱ ከደረሰ ከ13 ዓመት በኋላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙ የቀረበበት ጉዳይ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት የታየ ስለሆነ እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት ስለማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ይግባኙ አያስቀርብም የሚል ብይን ሰጥቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህም ብይን ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኙን አያስቀርብም ለማለት የሰጠው ምክንያት የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ከሰጠው ብይን ጋር የሚገናኝ አይደለም፣ በአሁን ተጠሪ የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ያደረገም አይደለም፤ ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት በመሆኑ ፍርዱን የሰጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 342 ላይ እንደተመለከተው የነገሩን ጭብጥ በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው ለማለት የሚቻልበት የህግ ምክንያት የለም፣ ይግባኙ አያስቀርብም ማለትም ፍርድ መስጠት ማለት አይደለም፤ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል ይግባኙ አያስቀርብም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የይግባኝ ክርክር ሰምቶ ሊሰጥ የሚችለውን ፍርድ መስጠቱ ትክክል አይደለም፤ በአጠቃላይ ፍ/ቤቱ የተከተለው አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ከተደነገገው የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት የወጣ በመሆኑ ይግባኙ የቀረበለት የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ተሽሯል፣ የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ብይን በሰጠበት የይርጋ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ/ውሳኔ/ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ተመልሶለታል በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን መልስ ሰጭን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት የሰረዘው በመሆኑ በዚህ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ሁለተኛ ይግባኝ



ለፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ መታየቱ አግባብ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቶ የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት የታየ ስለሆነና እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት ስለማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ይግባኙን በብይን ሰርዞት በዚህ ብይን ላይ የቀረበለትን ይግባኝ የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎ በመመርመር የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮ የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ብይን በሰጠበት የይርጋ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ/ውሳኔ/ ይስጥ በማለት ጉዳዩን ለከፍ/ፍ/ቤት የመለሰው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት ወይም ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ መመርመር ከመጀመሩ በፊት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ የኖርበታል፡፡ የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎ በማየት ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ በመጀ/ደ/ፍ/ቤት ብይን ተሰጥቶበት ከፍ/ፍ/ቤትም በይግባኝ አይቶ ብይን የሰጠበት በመሆኑ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ. 25/1988 አንቀጽ 10/1/ መሠረት የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች (መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው) አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንጂ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት (የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት) ይህንን የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ አይቶ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24699 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን የቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 29761

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
መስፍን እቁበዮናስ
ሂሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ዳባ ደበሌ - ቀረቡ
2ኛ .. ደምሴ በዳዳ ቀረቡ
3ኛ ወ/ሮ አለሚ ተ/ፃዲቅ ቀረቡ
4ኛ .. ደግነሽ ጫሞራ ቀረቡ
5ኛ ቄስ ኤፍሬም መኰንን ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች
1ኛ ወ/ሮ ሸዋማማሽ ደበበ
2ኛ ሻ/ቃ ጌቱ ደበበ } ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 03678 መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭዎች ለሰበሩ አቤቱታ መነሻ በሆነው ጉዳይ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን ክሱን በቅድሚያ ተቀብሎ ላየው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የአውራሻችን የአቶ ደበበ ተፈራ ንብረት የሆነውን በአቃቂ ከተማ የሚገኘውን የወፍጮ ቤት ድርጅት በወቅቱ የነበሩት የቀበሌ ተመራጮች ከፋፍለው ለአምስቱም አመልካwች በመስጠታቸው እና አውራሻችን ከዚሁ ድርጅት በቀር ሌላ ያልነበራቸው መሆኑን በማረጋገጥ